

ECSU

Est.1995

BUILDING CAPACITIES IN THE PUBLIC SERVICE

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
# Ethiopian Civil Service University

Monthly Newsletter
July 2016
Vol.13 No.1

***Public Relations Directorate***

## Ethiopian Civil Service University Colorfully Graduates Students





Ethiopian Civil Service University colorfully graduated 1740 students with PhD, Masters and Bachelor degrees on July 16, 2016 at Abay Hall in the main campus of the University in the presence of Her Excellency W/ro Aster Mamo with the rank of Deputy Prime Minister Coordinator of Good Governance and Reform Cluster and Minister of the Public Service and Human Resource Development, other higher government officials, representatives of the embassies and the University community.

Guest of honor Her Excellency W/ro Aster Mamo said it is great to attend the day when the university community celebrate success. She congratulated the University community for the achievements. " On behalf the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, I promise to extend support in your efforts to fulfill your goals," she said. " To speed up our Renaissance your role is indispensable. The government is giving great emphases to strengthen the capacity of human resource development. We give priority to building the capacity of the public service to realize our development policies and strategies", W/ro Aster underscored.

Ethiopian Civil Service University has open a new chapter and is helping us achieve our goals of building the capacity of the public service through specialized education and training. The University is also working to support and actively involve in the economic development by building a strong public service in the country. Our higher learning institutions work relentlessly to implement the second growth and transformation plan and uphold our transformation by conducting problem solving researches and participating in the community development, she added.



In his opening remarks, Ethiopian Civil Service University President, Professor

## Our Vision

**To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country**

## Our Mission

**Enhancing the service orientation , transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education, Training, Consultancy, Research and Community Services.**

## Our Values

- **Customer Focus**
- **Commitment**
- **Continuous Learning**
- **Welcoming Diversity**
- **Attention to the Disadvantaged**
- **Participatory leadership**
- **Collaboration**

Fekadu Beyene congratulated the graduates for their achievements. He said you are climbing new heights of success; you are primary drivers of the economic development of the country. The knowledge ,skills and attitudes you have got while staying in our university should bring about change in the real world .You are ambassadors for our university and you could play a great role in building democratic society, peace and development in every aspect of the society`s life.

'ECSU has played a key role in the develop-



ment of the civil service and in building the capacity of government officials in the country. Besides, we are giving scholarship to neighboring countries` civil servants to strengthen the already existing people to people relations. We work hard to make our university become center of excellence in public service capacity building, he added. Finally he thanked the university community, partners and the graduation committee.

Guest of honor , H.E W/ro Aster Mamo, handed out awards and degrees for graduates and



Gold medals to outstanding graduates. The graduates presented a gift to the university. The University graduated 1740 civil servants with



first , second and third degrees and among the total number of graduates in the 2016 academic year, 539 were female.

The programs concluded with the national anthem of Federal Democratic Republic of Ethiopia.

## ECSU Holds Second National Conference

Ethiopian Civil Service University Research and Publication Coordination Office in collaboration with Center for Research in Ethics and Integrity, organized a two days national conference from June27 to 28/2016 in the University`s Hidase Hall with a theme "Public Sector Transformation and Development"

In his welcoming speech Ato Birhanu Belayneh



Vice President for Research and Community Services appreciated the organizing committee of the research conference. He also said that the role of research in supporting the ongoing transformation and development is believed to be immense. We academicians are expected to respond to the bottlenecks in public sector capacity building and discharge our responsibilities not only as citizens of the nation but also as professionals. Therefore , ESCU, with the mandate of building the capacities of public sectors has been doing its level best to enhance the ongoing all rounded development in the country and contributed a great share for the recorded achievement.

He also pointed out that as part of its ongoing effort to become center for excellence in public services capacity building in Africa by 2025. So the

University has given emphasis to researches and to this effect, the University sponsored more than 40 problem solving projects. Among these, 24 researches output are selected to be presented in this national conference. In his final message he requested all the participants to take this conference as learning and experience sharing opportunity as well as an avenue to refine and improve the quality of research outputs.



Dr. Samson Kassahun, Vice President for Academic Affairs, on his part welcomed all the participants to the second national conference." Besides building the capacity of the civil servants in specialized education and trainings, ECSU has organized its research wing and has established two research centers with the objective of conducting problem solving and relevant researches on the public service which are important to improve the civil service system Dr. Samson said.

He also added that the research papers which were going to be presented in two categories, "Ethics, Public Service Reform and Capacity Building" and "Development , Public Policy , Governance and Cross Cutting Issues" could contribute significantly on the improvement of the civil service reform programs. Besides these research papers were believed to induce further discussion, participation, and contribute to better understand the public service transformation and development in Ethiopia.

On the two days conference 30 research papers on selected research topics were presented by ECSU and other Higher Educational Institutions scholars. ECSU academic staff, students, scholars from different higher educational institutions and stake holders participated in the conference.

## Puntland Delegates Visit ECSU

A high level delegation from Puntland visited the ECSU for two days (June 16 and 17,2016). The delegates were received by the top management of the university and had attended a special meeting with the President of ECSU. They also attended comprehensive PowerPoint presentations on Ethiopia, the Ethiopian public service, as well as the establishment and growth of the ECSU, which were presented by Professor Fekadu Beyene, President of ECSU, and Dr. Mulugeta Debebe, Vice President of Training and Consultancy, ECSU and moderated by Ato Seifu Bekuretsion, Head of the International Relations, ECSU. A tour of the ECSU premises was also part of the programme.

A draft memorandum of understanding was also deliberated on which included area of cooperation between the ECSU and Puntland, including:



Development and implementation of training modules, designing Specialized Short-term training courses, Provision of support to existing training institutions in Puntland, Provision of long – term training to develop professionals in Financial Management, Procurement, and Monitoring and Evaluation, training and development of advisory services to civil servants, and others.

The delegation was composed of: The Minister of Labor, Director of Human Resources Development, Director of Training, Project Chairperson, Vice Chancellor, Deputy Vice Chancellor, Project Coordinator, and Project Communication Specialist. The visit was organized by the World Bank Group and the Federal State of Puntland in cooperation with the International Relations Office of ECSU

## የ2008 ዓ.ም. የስራ አፈጻጸም ግምገማ ቅኝት

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ከ2003- 2007 ዓመት ምህረት የቆየ እስትራቴጂክ እቅድ አውጥቶ በስፔሻላይዝድ ትምህርት ፕሮግራሞች፣ በአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎቶች  በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ለውጥ ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ሲያበረክት እንደቆየ የሚታወቅ ነው፡፡ካለፉት አፈጻጸሞች በመነሳት እና ከልዩ ልዩ ሴክተሮች ጋር የተዛመደ እና ከሀገሪቱ የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተቀዳ የአምስት አመት እስትራቴጂክ እቅድ ከ2008 – 2012  በማውጣትና ከዚሁ እቅድ የተወሰደ የአንድ አመት እቅድ ለ2008 ዓ.ም አውጥቶ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በተለይ በ2008 ዓ.ም  ያከናወናቸውን ተግባራትና የተገኙ ውጤቶችን በየክፍሉ ከገመገመ በኋላ አጠቃላይ ክንውኖችን  የያዘ ሪፖርት  ሐምሌ 6 ቀን 2008 ዓ ም  በአባይ አዳራሽ ለመላው የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ቀርቧል፡፡ ሪፖርቱን ያቀረቡት አቶ ታመነ ጫልቺሳ የተቋማዊ እቅድና ግምገማ ጽ/ቤት ዳይሬክተር ሲሆኑ በሪፖርቱ ላይ የተለያዩ ሐሳቦችና አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ የሪፖርቱ አጠቃላይ ይዘትም አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በህግ በተሰጠው ተልእኮ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ሴክተር የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የፐብሊክሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የ2008 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ፣ የዩኒቨርሲቲው የ2008-2012 የዓምስት ዓመት ትራቴጂክ እቅድ እና የዩኒቨርሲቲው የ2007ዓ ም በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸሞችን እንደመነሻ በመውሰድ  በ2008 በጀት ዓመት የተሟላ ቁመና ያለው የለውጥ ሠራዊት መገንባትንና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈን በቁልፍ ተግባርነት በመያዝ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከቱ እንዲሁም በስነ ምግባሩ ያደገና የተሻለ እንዲሆን በማድረግ የተሰጠውን ተልዕኮ ብሎም የአገራችንን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት እንዲችል የማብቃት ሥራ በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን ጥረት መደረጉ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የተሟላ ቁመና ያለው የለውጥ ሰራዊትን ለመገንባት እንዲቻል 120 የለውጥ ቡድኖች እና በድምሩ 598 የሚሆኑ የመምህራን፣ የሠራተኞችና የተማሪዎች የ1ለ5 ቡድኖች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡ በለውጥ ቡድኖችም ግንባር ቀደሞችን የመለየት ተግባር የመምህራንና የሠራተኞች ከታቀደው 60% ውስጥ 33.3%፤ በተማሪዎችም ከታቀደው 50% ውስጥ 12.74% ለመለየት ተችሏል፡፡የለውጥ አፈጻጸምን ለማረጋገጥ በአስተዳደርና በአካዳሚክ ዘርፎች ላይ ሁለት ጊዜ የሱፐርቪዥን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ አንድ ጊዜ ብቻ የተከናወነ መሆኑንና የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር በየወሩ ከመምህራን፣ ከሠራተኞችና ከተማሪዎች ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ ለሚነሱት ችግሮች በየጊዜው መፍትሔ እንዲያገኙ በማድረግ በአፈጻጸማቸው ላይ ከፍተኛ ክትትል መደረጉንም ሪፖርቱ ይጠቅሳል፡፡

**መልካም አስተዳደርን ማስፈንና የኪራይ ሰብሳቢነትን በመታገል ረገድ** የለውጥና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ውይይትም የተደረገበት ሲሆን ለአፈጻጸም እንዲያመችና በየሥራ ክፍሉእንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡በለውጥ ሠራዊት ቡድኖች ውይይት በግለሰቦችም ሆነ በድርጅቶች የሚቀርቡትን ቅሬታዎች እንዲፈቱ ተደርገዋል፡፡ቅሬታዎች ለመፍታት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የአካዳሚክ ቅሬታ ሰሚ ቡድን የተቋቋመ ሲሆን በአስተዳደር ዘርፉ በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ሌላ ቅሬታ ሰሚ ተቋቁሟል፡፡ለቅሬታ ማቅረቢያ የሚሆኑ 16 የሃሳብ መስጫ ሳጥኖችም በየቦታው ተቀምጠው ክትትል እየተደረገባቸው ይገኛል፡፡የዩኒቨርሲቲው የዜጎች ቻርተር እንደገና የመከለስ ሥራ የተከናወነ ሲሆን ውይይት ተደርጎበት የማጽደቅ ሥራ ይቀራል፡፡በተማሪዎችዎችና በሰራተኞች ይነሱ የነበሩ የአገልግሎትና የጥቅማ ጥቅም ቅሬታዎችም ተፈተዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲዉ ባሉ በተለያዩ መድረኮች የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች እርምት የሚወስድ ፈፃሚ ክፍሎችም የሚዘረዝር ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ተሰራጭቷል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት ዓመት ውስጥ የተለያዩ አበይት ተግባራትን በዕቅድ ይዞ ሲያከናወን የቆየ መሆኑን የጠቀሰው ሪፖርቱ የፐብሊክ ሴክተር ዕርካታን በሚመለከት የውስጥና የውጭ የዳሰሳ ጥናቶችን በማድረግበአፈጻጸሙ ረገድ በትምህርት 82% ለማድረስ ታቅዶ ውጤቱን ለማጠቃለል በሂደት ላይ እንደሚገኝ፤ ለዳሰሳ ጥናቱ መረጃ ከተለየዩ ክልሎችና ተቋማት መሰብሰቡንና በማማከር ረገድም 75% ታቅዶ የመረጃ ማሰባሰቢያ ሰነድ የተዘጋጀ ቢሆንም አለመተግበሩን፣በማህበረሰብ አገልግሎት የማህበረሰቡ ዕርካታ 60%ለማድረስ ታቅዶ 90% መገኘቱ ጠቅሷል፡፡በውስጥ ተገልጋዮች በኩል የተማሪዎችን ዕርካታ 85% ለማድረስ ታቅዶ 77.4% ሲገኝ፡ ሠልጣኞችን ዕርካታ ደግሞ 91% ለማድረስ ታቅዶ 93.5% ተገኝቷል፡፡

በትምህርት ፕሮግራሞችም ለ2008 በጀት ዓመት ነባርና አዲስ ተማሪዎችን በመመዝገብ በመጀመሪያ በሁለተኛና  በሶስተኛ ዲግሪ በአጠቃላይ 4866 ( ወ 3400፣ ሴ 1466) በማስተማር ላይ ይገኝ እንደነበረ ተገልጿ፡፡ በበጀት ዓመቱ በሁለት የምረቃ ስነ ስርዓቶች 1312 ተማሪዎችን በቅድመ ምረቃ 991 ተማሪዎችን ደግሞ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር አስመርቋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የምስራቅ አፍሪካ ጎረቤት አገራትን የሲቪል ሰርቫንት አቅም ግንባታን ከመደገፍ አኳያ ነጻ የትምህርት ዕድል በመስጠት ለመርዳት አገሪቷ ከያዘችው አቅጣጫ አንጻር ከሱዳን፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከጁቡቲ፣ ከሶማሌ ላንድ፣ ከፑንትላንድ፣ ከሶማሊያ፣ ከኬንያ፣ ከሩዋንዳ፣ ከቡሩንዲና ኡጋንዳ 182 ተማሪዎችን በመቀበል 130 በማስተርስ፣ 52 በመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷቸው በመመማር

ላይ የነበሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 34 ተማሪዎች ማለትም 18በማስተርስ ፣ 16በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀዋል፡፡

የትምህርት ፕሮግራሞች ሞጁላራይዝድ በማድረግ፤ ተማሪዎችም በኦንላይን እንዲጠቀሙበት በማድረግ፡የመስከ ልምምዶችን በማመቻቸት ፤ከታዳጊ ክልል የመጡና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ሴት ተማሪዎችን ለማገዝ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከአዲስ አበባ መስተዳደር ጋር በመተባበር በመጀመሪያ ዲግሪ በማታው ትምህርት ፕሮግራም278 ተማሪዎችን ተቀብሏል፡፡ በሊደርሽፕ በሁለተኛ ዲግሪ ከፍተኛ መኮንኖችን ለማስተማር ከሀገር መካለከያ ሚኒስቴር ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ተፈፅሟል፡፡ዩንቨርሲቲው አሁን ከሚሰጣቸው ሶስት የዶክትሬት ፕሮግራሞች በተጨማሪ ሌላ ሶስት ፕሮገራሞችን ለመከፈት ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጋር ዝግጅት ተደርጎ ለ2009 የትምህርት ዘመን ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች በሚመለከት ዩኒቨርሲቲውበፐብሊክ ሴክተሩን አመራርና አሰራር ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በጥናትና ምርምር ለመፍታት ከልዩ ልዩ ማዕከላትና ኢንስቲትዩቶች ጋራ በመተባበር የ37 ምርምር ፕሮፓዛላቸው ጸድቀውና በበጀት ተደግፈው ወደ ሥራ መገባቱንና የ2 ጥናትና ምርምር ሥራዎች ተጠናቀው ውጤታቸው መቅረቡን፤የ11 ጥናትና ምርምሮች ዳታ የማሰባሰብ ስራ ተጠናቆ ወደ ዳታ ትንታኔ ሪፖርት ዝግጅት መገባቱንና የ24 ጥናትና ምርምሮች ዳታ የማሰባሰብ ስራ መጀመሩንም ሪፖረቱ ያትታል፡፡ሶስት ሰሚናሮችና አንድ ኮንፈረንስም ተካሄደዋል፡፡ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴርና ከፌዴራል ሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በጋራ ሁለት የምርምር ምክረ ሃሳቦች በመጽደቃቸው በበጀት ተደግፈው ወደሥራ ተገብተዋል፡፡በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በተመረጡ ሶስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ጥናትም ተከናውኗል፡፡

***በተጠናቀቀው በጀት ዓመት*** ለ4023 ሠልጣኞች የተለያዩ ሥልጠናዎች ፡በማማከር አገልግሎትም***ደግሞ*** ለ3 ተቋማት***የ***ማማከር አገልግሎትም ተሰጥተዋል**፡፡**ለ31 የተለያዩ ተቋማት በ171 የሥራ መደቦች ላይ ለ675 ተወዳዳሪዎች የቅጥርና የደረጃ ዕድገት የችሎታ መመዘኛ ፈተና ተሰጥቷል፣ ውጤቱም ተጠናቅሮ ለየተቋማቱ ተልኳል፡፡የስርዓተ ጾታና HIV/AIDS እና የአካል ጉዳተኞች ከበባት ተቋቁመው በተለያየ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እየሰሩ ሲሆን ፣2 ምርጥ ተሞክሮ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማምጣት ግንዛቤን ማስፋት ተችሏል፡፡ በሥርዓተ ጾታ እና HIV/AIDS ላይ የአመራሮችንና ሠራተኞችን አመለካከት በእውቀትና በክህሎት የመገንባት ፣አካል ጉዳተኞችን በማገዝ በኩልም በርካታ ስራዎች መከናወናቸው ተጠቅሷል፡፡

**የውስጥ አቅም ግንባታ *ሥራዎችን* በሚመለከት**የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሠራተኞች በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ለማሳደግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ለዩኒቨርሲቲው መምህራንናሠራተኞች የተለያዩ ሥልጠናዎችና ለአካዳሚክ ሠራተኞች በጥናትና ምርምር ክህሎት ማሳደጊያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ሶስት የድህረ ምረቃ ትምህርት ካሪኩለም ቀረጻም ተከናውኖ ጸድቋል፡፡የመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች አቅምን ለማሳደግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት በተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች በድምሩ 53 መምህራንና ሰራተኞች ትምህርታቸውን በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ የቢኤስሲ በአዉቶሜሽን ሲስተሙን ተግባራዊ ለማድረግ በማቀድ ዕቅዱንም በሲስተሙ ላይ ወደ ግለሰብ ፈጻሚ ለማውረድ እንዲቻል የሰዉ ሀብት መረጃ በሙሉ ወደ ሲስተሙ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ለአካዳሚክና አስተዳደር የሥራ ዳይሬክተሮች ሥልጠናም ተሰጥቷቸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከፍርድ ቤት መለስ ያሉ ጉዳዮችን በድርድር በመፍታት ብር 325,882.43 ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙትን ክንውኖች እንዲሁም የተገኙ ውጤቶችን ለሌሎች ለማሳወቅ የተዘጋጁ 5 ወርሃዊ መጽሔቶች 500 ኮፒና አንድ የግማሽ ዓመት መጽሄትና ብሮሹሮች ተሰራጭተዋል፤ ዜናዎች በዌብ ሳይት እና በልየ ልዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ እንዲለቀቁ ተደርጓል፡፡የተለያዩ መ/ቤቶች የዩኒቨርሲቲውን የሥልጠና ፋሲሊቲዎችን በመጠቀም ለ42,241 እንግዶች የሥልጠና ፋሲሊቲና የመስተንግዶ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲውን የሥጋት አስተዳደርን ለማወቅ እንዲቻል የሥጋት ዳሰሳ የሚያከናውን ቡድንም ተቋቁሞ መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ተጠናቋል፡፡

**የበጀት አጠቃቀምና የውስጥ ገቢን በሚመለከት** በበጀት ዓመቱ ዩኒቨርሲቲው ከሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ጥቅል ሽያጭ በድምሩ ብር41,879,253የውስጥ ገቢ ተገኝቷል፡፡የዩኒቨርሲቲው የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ በዋና ኦዲተር ተመርምሮ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረጉትአንዳንድ ግኝቶች በስተቀር የበጀት አጠቃቀሙ የመንግስት የፋይናንስ ሥርዓት አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን በመከተል ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ በሪፖርቱ ቀርቧል፡፡እነዚህ የቀረቡትን ግኝቶችን ለማስተካከል ዩኒቨርሲቲው የድርጊት መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ለዋና ኦዲተር መ/ቤት አቅርቧል፡፡ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለካፒታል በጀት ከተፈቀደው ብር140,000,000 ውስጥ 79,537,473.38 (57%) ሥራ ላይ

ውሏል፡፡ ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው -ከግምጃ ቤት ብር158,691,300 ውስጥ ብር106,707,873.88 (67%) ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ከዉስጥ ገቢ 33,390,100 ውስጥ ብር 32,319,569.08 (97%) ሥራ ላይ ውሏል፣ ከዓመቱ አጠቃላይ በጀት ብር 332,181,400 ውስጥ 221,867,445 (67%) በጀት ሥራ ላይ ውሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የበጀት አጠቃቀሙ ዝቅ ሊል የቻለበት ምክንያትም ክፍያዎች ተፈጽመው በማስረጀዎች ባለመወራረዳቸው ፤ግዥዎቻችን በመዘገየታቸው፣ አንዳንድ ጨረታዎች እንዲዘገዩና እንዲሰረዙ በመደረጋቸው አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት የተለያዩ የምግብና የመገልገያ ቁሳቁሶችን በለማቅረባቸውመሆኑ ተጠቅሷል፡፡

**የልምድ ልውውጥ አገልግሎት እና ምርጥ ተሞክሮዎች በማጋራት ሂደትም** በበጀት ዓመቱ የዕቅድ አፈጻጸም ውስጥ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣የኦሮሚያ ፐብሊክ ሰርቪስ ኮሌጅንጨምሮ ለ23 ተቋማት በልዩልዩ አርዕስት ላይ የልምድ የተሞክሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡

**በበጀት ዓመቱ የታዩት ደካማ ጎኖችም** የአመለካከት ለውጥ የሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ የ1ለ5 የለውጥ ሠራዊት አደረጃጀት የአንዳንድ አካላት ተሳትፎቸው የሚጠበቀውን ያህል አለመሆን፣ግንባር ቀደሞችን የመለየት ሥራ በተጠናከረ መልኩ አለመሰራት፣ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደው በጀት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ አለመዋል፣ የተጠናቀቁ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ውጤታቸው ታትሞ አለመውጣት፣ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንደ ሪፖርቱ ዘገባ በአንዳንድ የሥራ መደቦች ላይ ለቅጥር ተደጋጋሚ ማስታወቂያ ቢወጣም ተወዳዳሪ ያለመገኘት፤ግዥዎች ላይ የዕቃ አቅርቦት ማዘግየትና የጥራት ችግር የመብራት መቆራረጥ ፤ዩኒቨርሲቲው ያለበት የቦታ ጥበት፣ በአንዳንድ ተቋማት በሚመጣ አስገዳጅ የፋሲሊት መጠቀም ጥያቄ ምክንያት ዩኒቨርሲቲው በዕቅድ ያዛቸውን ሥልጠናዎችን ለመስጠትና ከሌሎች ተቋማት ጋር አስቀድሞ የገባባቸውን ግዴታዎችን ለመወጣት አለመቻል በበጀት ዓመቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ለእነዚህ ተግዳሮቶችምየተለያዩ መፍትሔዎች የተወሰዱ ሲሆኑ ለአብነት ያህልምበለውጥ ሠራዊት የውይይት መድረክ ላይ የቡድን አባላት እንዲገመገሙ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፣ጥራት የጎደለውን ዕቃ በሚያቀርቡ አቅራቢዎች ላይ ክትትል እንዲደረግና የኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች ተቋቁመው ጥራቱን አንዲቆጣጠሩ ተደርጓል፡፡የመብራት መቆራረጥ ችግርን ለመቅረፍ ግቢ ውስጥ የነበረውን ጄኔሬተር ስራ ላይ ለማዋልና ሌሎች ጄኔሬተሮችን ለመግዛት የሚቻልበት ሁኔታ እንዲመቻች የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል፣ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን የማስፋፊያ ቦታ ጥያቄ መፍትሔ እንዲያገኝ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችን ለማነጋገር ጥረት ተደርጓል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ ውስጥ በርካታ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችም አከናውኗል፡፡በልማታዊ መልካም አስተዳደርና የፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠርጥረት ተደርጓል፡፡ነባር የትምህርት ፕሮግራሞችን ማጠናከርና የፐብሊክ ሰርቪሱን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችሉ አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞችን መክፈት፤ለፐብሊክ ሰርቪሱ ጠቃሚና ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን ማካሄድ፣ የተጀመሩትንም ማጠናቀቅ፣ማሳተምና ማሰራጨት፣የሥልጠናና የማማከር አገልግሎቶችን ማስፋፋት፤የዩኒቨርሲቲው መምህራን በከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም ሰርቲፋይድ እንዲሆኑ ማስቻል ወዘተ በዩኒቨርስቲው የወደፊት የትኩረት አቅጣጫ ተደርገው የተወሰዱ ተግባራት መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡

ዝርዝር ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ ተሰበሳቢዎች የዩኒቨርሲቲውን ገፅታ ከመገንባት አኳያ ምን ስራ እየተሰራ እነዳለ፤የሴት መምህራን ቁጥር ዝቅተኛ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና ጥናትና ምርምር ላይ የሚታዩ አንዳንድ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ ጥያቄና አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡በአቅራቢዎች ችግር ምክንያትና በግዢ መዘግየት የተነሳ እየተፈጠረ ያለውን መጉላላት ዩኒቨረሲቲው ትኩረት እንዲሰጠው ተሰበሳቢዎች ጠይቀዋል፡፡ በበጀት አመቱ መጨረሻ ላይ የሚደረግ የግዢ ሂደትም መስተካከል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ የዩኒቨርስቲው የበጀት አጠቃቀምን አስመልክቶ 67% ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉ ተገቢ አለመሆኑና መስተካከል እንደሚገባው ተጠይቋል፡፡

በስብሰባው ማጠናቀቂያ ላይ የዩኒቨርስቲው ፕሬዚደንት ፐ/ር ፈቃዱ በየነ በዩኒቨርስቲው ያለው የሴት መምህራን ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ለወደፊት በስፋት እንደሚሰራበት ተናግረዋል፡፡በጀትንም አስመልክቶ በእስካሁኑ የፋይናንስ አጠቃቀም ጥሩ አለመሆኑን ጠቅሰው በቀጣዩ የበጀት ዓመት ባልተማከለ መንገድ የሚከናወን በመሆኑ እያንደዱ ክፍል የበጀት እቅዱን ባስቸኳይ እንዲያቀርብ አሳስበዋል፤እስከ መስከረም ወር ድረስም ለትምህርት የሚሆኑ ግብአቶችበሙሉ ለመግዛት ጥረት እንደሚደረግ፣ የግዢ አጽዳቂ ኮሚቴም እየተመለመለ እንደሆነእና አጠራጣሪ የሆኑ ግዢዎችንም ሰርዘናል ብለዋል፡፡ የምርምር ቴማቲክ አሪያዎችም በወርክሾፕ መለየት እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡፡ በገጽታ ግንባታ ረገድም የእኛ አምባሳደሮች ተማሪዎቻችን ናቸው እኛም ለተማሪዎችችን ሞዴል መሆን ይጠበቅብናል፡፡ በቅርብ ጊዜ አለማቀፍ ኮንፈረንስ ለማድረግ ጥረት እያደረግን ነው በዚህ መልክ እራሳችንን መግለጽ ይኖርብናል ከዚህ ውጪ የገጽታ ግንባታ ስራ የሁሉም ሰራተኛ የቤት ስራ መሆኑን ፕሮፌሰር ፈቃዱ ገልፀዋል፡፡